# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 23 ቀን 2006 ዓ.ም.
(May 1, 2014)

### *ለላብ አደሩና ለሠራተኛው ያለን ወገንተኝነት በመርህ ላይ የተመሰረተ ነው!!*
### *ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ቀንን አብረን እናክብር!*

የዘንድሮው የሚያዚያ 23 ቀን 2006 ዓ.ም (ሜይ 1/2014 ) ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን በተለያዩ አህጉራት ያሉ ላብ አደሮችና ሠራተኞች እንደሚገኙበት የፖለቲካ ምህዳር በዓሉን የተለያዩ ፕሮጋራሞችን፤ መግለጫዎችን፤ ትርዕኢቶችንና የተቃውሞ ሰልፎችን በማዘጋጀት ያከብሩታል። የዴሞክራሲ ሥርዓት በተገነባባቸውና መብቶቻቸው ሕጋዊ እውቅና አግኝተው በሚከበሩበት ሀገራት የወቅቱን በዓላቸውን የሚያከብሩት በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተውና አሁንም ድረስ ሊረጋጋ ባልቻለው የኤኮኖሚና የፋፍይናንስ ቀውስ አማካኝነት እየደረሰባቸው ያለውን የኤኮኖሚ ጉዳት ሊወገድ የሚችልበትን የራሳቸውን አማራጭ ፖሊሲ እየቀየሱ በመታገል ላይ እንደሆኑ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተለያዩ የዜና ተቋማት እየወጡ ያሉ መግለጫዎቻቸውና የራሳቸው ይፋዊ ጥያቄዎቻቸው የሚያመላክቱት ነው። በዓላቸውን በሚያከብሩበት ወቅት ደግሞ የበለጠ ክብደትና ጫና ሰጥተው ትግላቸውን ከምንጊዜውም በበለጠ አቀነባብረው የሚገልፁበትም ቀን ነው።

በታዳጊና በተለይም ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች በማይከበሩባቸው እንደ ኢትዮጵያ በመሰሉ ሀገራት ደግሞ ለላብ አደሩና ለሠራተኛው የሕብረተሰብ ክፍል በነፃ የመደራጀት መብት መከበርና ለኤኮኖሚ ጥቅሞቻቸው መሟላት ይፋዊም ሆነ የህቡዕ እንቅስቃሴዎች ያደርጋሉ። ከዚህም ባሻገር መሠረታዊ የሆነው የዴሞክራሲ ጥያቄን አስመልክቶ እንደ ሁኔታው አመቺነት ከሀገር ወዳዱ የሕብረተሰብ ክፍል ጋር በግምባር ቀደምትነት በማበርና በጋራ በመታገል የሚያከብሩት መሆናቸውም የሚታወቅ ነው።

የኢትዮጵያ ላብ አደሮችና ሠራተኞች ይህንን የራሳቸው የሆነ የበዓል ቀን የሚያከብሩት ለመብቶቻቸው መከበር በግንባር ቀደምትነት በመሰለፍ ሲታገሉ የተሰዉ መሪና ንቁ አባሎቻቸውን በመዘከር ጭምር ሲሆን በሌላ ሀገራትም ከሚገኙ ጭቁን ላብደሮችና ሠራተኞች ጋር ያላቸውን የትግል አንድነት በመግለፅም ጭምር ነው። ይህ መከበር ከጀመረ ከ120 አመት በላይ የሆነው የላባደሮችና የሠራተኞች ቀን ዛሬ በሀገራችን ሲከበር ቢያንስ ከ40 አመታት በላይ እንደሆነው የተለያዩ የፖለቲካ ድርሳናት የሚገልፁት ነው። ይህ በዓል የሚከበረው በተለይ እንደነአበራ ገሙ፤ ማርቆስ ሀጎስ ዳሮ ነጋሽን የመሰሉና ሌሎቹንም በትግል የተሰዉ መሪዎቻቸውን፣ ንቁ አባሎቻቸውን ጭምር የትግል ታሪካቸውን ችቦ ከፍ አድርጎ በማብራት ብቻ ሳይሆን ላለፉት በርካታ ዓመታት ሠራተኛው ያደረጋቸውን ተጋድሎዎች በማስታወስም ነው። እንዲሁም የት ደርሰናል? ምንስ ይቀረናል? የሚሉትንና ሌሎችንም ላባደር ነክ ርዕሶችን በጥልቀት በመዳሰስና መፍትሄ በማፈላለግ ጭምር ነው የሚያከብሩት። በዛሬው ዕለት ይህንን ቀን ስናከብርና ስንዘከር ከሕሊናችን ምንጊዜም የማይጠፋውንና ተተኪ ትውልድ ምንጊዜም ሊያስታውሰው የሚገባው፣ በወታደራዊው አምባገነን አገዛዝ ከ1500 በላይ የሆኑ ወጣት ተማሪዎች፤ መምህራን፤ ሠራተኞችና ላብ አደሮች እንዲሁም የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ዘግናኝና አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ በግፍ የተጨፈጨፉበትን ሚያዚያ 1ን በማስታወስ ነው። ይህንንም በያለንበት ሻማ በማብራት የሀዘን እንባችንን በማፍሰስ ነው የምናስታውሰው።

በሀገራችን ነፃነቱ የተጠበቀ፤ እንደ አይን ብሌናቸው የሚሳሱለት፤ የራሳቸውና በራሳቸው ሙሉ ኃላፊነት የሚተዳደሩበትና መብቶቻቸውን ለማስከበር በፅናት ቆሞ የሚታገልና የሚያታግል ድርጅታቸውን መልሶ የማቋቋም ፍላጎታቸውና በርካታ መስዋዕትም የከፈሉበት መርህ ቃል ዛሬ ከምንጊዜውም በላይ አፋጣኝ መልስ የሚሻበት ወቅት ላይ እንደሚገኙ እሙን ነው። ይህም ሲባል አለምክንያት አይደለም። የወያኔ አገዛዝ ሥልጣኑን ለመቆጣጠር ከቻለ ጀምሮ ላለፉት 22 አመታት በነፃ የመደራጀት መብታቸውን በመፃረር አባሎቻቸውን በተለያዩ

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

እንግልቶች፣ ግድያ፣ እስራትና ለስደት በመዳረግ አዳከሞ ለራሱ ተለጣፊ የሆነ ድርጅት በጫንቃቸው ላይ አንግሶባቸው ከሀገር በቀልና ባዕዳን ደጋፊዎቹ ጋር በመተባበር ካለፉት አገዛዞች በበለጠ ላብ አደሩንና የሰራተኛውን ሕብረተሰብ እየበደለ፣ እየጨቆነና እየበዘበዘ ይገኛል። በተለያዩ የፋብሪካ ሰራተኞች ላይ የተካሄዱት የተለያዩ እንግልቶች ከራሳቸው አልፎ በቤተሰቦቻቸው ላይ ያስከተሉት የጭንቀት ኑሮ ዘንድሮም በከፋ ደረጃ ቀጥሎ መገኘቱ የሚታይ ነው።

የአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች የላባደሩን ነፃነት ደፍጥጠው በሙስና እጅጉኑ ተጨማልቀው ባካበቱት ኃብት በጨቀየ ሁናቴ እየተንደላቀቁ ባሉበት እንደ ቻይና ሰራተኛ አትሰራም እያሉ ሰብአዊ ክብሩን በሚያዋርድና የጠላትነት መንፈስ በተሞላበት መልክ ይዘልፉታል። በአሰሪዎቹ ሲደበደብ ለመብቱ መከበር የቆሙ አይደሉምናም ከአሰሪዎቹ ጋር ተዳብለው አብረው ይወቅጡታል። አልሆን ቅጣትም ያሳርፉበታል። ኤኮኖሚውን አሳደግን እያሉ በምሳሌነት ከሚያሳዩዋቸው ሕንፃ በስተጀርባና በየመንገዱ ዳርቻ ከነቤተሰቦቻቸው ለጎዳና ተዳዳሪነት የተዳረጉትን በርካታ ሰራተኞችን በፕሮፓጋንዳ ብዛት ለመሸፋፈን ሲጥሩ ይታያሉ። የተራቡ አንጀታቸውን፣ የተጠሙ ጉሮሮአቸውን በአይነ ሕሊናቸው ለማየት ይቀፋቸዋል። ኤኮኖሚ አድጓል በማለት መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ በነዙበትና እነሱ ራሳቸው ሚሊየነሮች የሆኑበትን ሕዝብ እንደተጠቀመ አድርገው ሲለፍፉ ብዙሃን ሰራተኛ እየተቆራረጠ ባለ የውሃና የኤሌክትሪክ ኃይል ምክንያት ሰራተኛው ያለምንም ካሳ በአሰሪዎቹ እየተባረረ ለከፋ ድህነት መዳረጉ አይታያቸውም።

በተስፋ ሊደልሉበት ከሚጥሩበት የእድገት ጀርባ ሽፋን የላባደሩንና የሰራተኞችን ጉስቁልናና ስቃይ እያበረከተ የሚገኘውን የገቢ እጦት በስፋት መንሰራፋቱን አይመለከቱም። ባዕዳኖች ለውጭ ዜጎች ባልተፈቀዱ ሥራዎች ላይ እየተሰማሩ ኃብት በገፍ ሲያካብቱ ላብ አደሩና ሰራተኛው ይህንን እንዳይከላከልና የሀገር ባለቤትነቱን በተግባር እንዳያስረግጥ በጠብመንጃ ኃይል መብቱን ገፈውታል። በአሰሪዎችና በሰራተኞች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ከሳሽና ፈራጅ ራሱ በመሆኑ ሂደቱ አጅግ በለጠጠ ሁኔታ ከመጓተቱ ሌላ የኋላ ኋላ ፍትህ እየተጓደለ ያለበት በመሆኑ ጭንቁን ይበልጥ አባብሰውበታል። ሰራተኛውን ለመደለልና የሚደርስበትን ተቃውሞ ያለዝብልኛል በሚል ከመብት ጋር የተያያዙ በርካታ የላባደሩና የሰራተኛ ጥያቄዎችን ሰምተው አጣርተው ትክክለኛ ብይን ይሰጣሉ ተብሎ ያቋቋማቸው ተቋማት ይበልጡኑ የሚበድሉት እንጂ የሚጠቅሙት ሆነው አልተገኙም። በኑሮ ውድነትና ያለ አግባብ በሚደረጉ የተለያዩ የታክስና የግብር ጭማሪዎች እዚህ ግቢ በማትባል እንዲያውም የመግዛት አቅሙ በየጊዜው እያሽቆለቆለ ባለቺው ደሞዙ ሰራተኛውና ላብ አደሩ ይበልጥ እየተጉላላ ይገኛል። በተለያዩ ጊዜያት የደረሰባቸው የበደል እርምጃ በአሰፈሪና በሚያሳዝን ሰቀቀን ውስጥ ተሸማቀው እንዲኖሩ ዳርጓቸዋል። እርስ በርስ እንዳይተማመኑም ሆን ብሎ ለመከፋፈል ያመቸው ዘንዳም የጥላቻ ፖለቲካ በመሃላቸው በመንዛት ብቻ ሳይሆን እንድነታቸውንም መልሰው እንዳይገነቡ የጎሳ መርዝ ነስንሶባቸዋል። ባጠቃላይ ላብ አደሩና ሰራተኛው እየተራበ፣ እየተጠማና እየታረዘ የሚቀመስ አጥቶ አይኖሩ ኑሮን በመግፋት ላይ የሚገኝ ነው።

በመሆኑም በዛሬው እለት ይህንን በአላቸውን እንደ አመቺነቱ በተለያዩ ሁናቴዎች በሚያከብሩበት ወቅት በነሱ ላይ እየደረሰ ያለውን ብዝበዛ፣ ጭቆናና በደል አጥብቆ በመቃወምና ለዚህ የዳረጋቸውን አገዛዝ ለማስወገድ በሚያደርጉት ያላሰለሰ ቆራጥ ትግላቸውም ከጎናቸው በመቆምና የትግል አንድነታችንን በማረጋገጥ ነው። ኢሕአፓ ከአመሰራረቱ ለላብ አደሩና ለሰራተኛው መብትና ጥቅም እንዲከበር የቆመ በመሆኑ የነሱ ነፃነት ባልተከበረበት የሌላውም ሕብረተሰብ ነጻነት ሊረጋገጥ እንደማይችል የፀና እምነቱ ነው። በመሆኑም ይህንን የነሱን ትግል በመደገፍ ለጋራ ስኬት በጋራ እንድንደርስ ይቻለን ዘንዳ በዛሬው እለትም ኢሕአፓ የትግል ጥሪውን አበክሮ ያቀርባል።

የላባደሩና የሰራተኛው ትግል ይቀጥላል
በጋራ ትግላችንም እናቸንፋለን!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France